DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

# የ DC ለመስማት የሚያግዝ መሳሪያ ድጋፍ እቅድ መረጃ

## ስለ ፕሮግራሙ

(DC Health)የኮሎምቢያ አውራጃ የጤና ክፍል Hearing Aid Assistance Program (HAAP) (ለመስሚያ የሚያግዝ መሳሪያ ድጋፍ እቅድ) በቤተሰብ ደረጃ አመታዊ ገቢያቸው ከ $100,000 የሚያንስ፣ የአውራጃው ነዋሪዎች፣ለመስማት የሚያግዝ መሳሪያ መግዣ ተመጣጣኝ ማካካሻ እስከ $500 ያቀርባል።

በ ጁን 1፣2018 እና በሴፕቴምበር 1፣ 2020 መካካል ለመስማት የሚያግዝ መሳሪያ  የገዙ ነዋሪዎች ማካካሻ ለመቀበል ብቁ ናቸው። ለመስሚያ የሚያግዝ መሳሪያ ማካካሻ   በኪስ ወጪው  ዋጋ ላይ እና በሚገኘው የርዳታ ገንዘብ በመመርኮዝ  በአንድ አመልካች እስከ $500  ድረስ ይገኛል ።

## የፕሮግራም ብቃቶች

ለማካካሻ ብቁ ለመሆን፣ አመልካቹ የአውራጃ ነዋሪ እና ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን ወይም ብዙውን ማሟላት አለበት፣

- እድሜ 0- 14 አመት የሆነ
- ከ 65 እድሜ ወይም ከዛ በላይ የሆነ
- የአካል ጉድለት ያለበት፣
- በቤተሰብ ደረጃ አመታዊ የተጣራ ገቢው ከ$100,000 ያነስ የሆነ።

ማካካሻ ለመቀበል፣ አመልካቹ የኮሎምቢያ አውራጃ HAAP (ለመስሚያ የሚያግዝ መሳሪያ  ድጋፍ እቅድ) ማመልከቻን ሁሉንም ሊሞሉ ይገባል። ማመልከቻው ከሚከተለው አስፈላጊ ሰነዶች ጋር አብሮ መያያዝ አለበት፣

- የአውራጃው ነዋሪነት ማረጋገጫ፣
- የገቢ ማረጋገጫ፣
- ለመስሚያ የሚያግዝ መሳሪያ የተገዛበት ማረጋገጫ፣ እና
- የመስማት ችግር ከዶክተ ማረጋገጫ።

## እንዴት ነው ማመልከቻ የማስገባው

የማካካሻ ማመከቻ ለማስገባት፣

- ይጎብኙ https://dchealth.dc.gov/page/health-care-access-bureau ማመልከቻውን ለመሙላት።
- ይደውሉ (202) 656-3027 ወይም በኢሜል tmoses@smsllcgroup.com  የወረቀት ማመልከቻ ለመጠየቅ።